# በቶሮንቶ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የድጋፍ ኮሚቴ በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የተደረገ ውይይትና የአቋም መግለጫ

መስከረም 11፣ 1998

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በካናዳ ቶሮንቶ ከተማ ዘሬ መስከረም 8 ቀን 1998 በጠራው ህዘባዊ ስብሰባ ላይ የተገኘን ኢትዮጵያዊያን ሰለ ሀገራችን ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ ለአራት ሰዓት ያህል ውይይት አካሂደናል፡፡ በስበሰባው ላይ በእንግድነት በመገኘት በሰሜን አሜሪካ የኢዴኃኅ ዋና ፀሀፊ የመቶ አለቃ አያልሰው ደሴ እና በከተማችን የኢዴኃኅ የድጋፍ ኮሚቴ አባላት ያደረጉትን ገለፃ አዳምጠናል፡፡

የመለስና የግብረ አበሮቹ ቡድን የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦቱ ምርጫ የሰጠውን ድምፅ ስለመዝረፉ እና የሰብአዊ መብት ስለመጣሱ የሀሳብ ልውውጥ አድርገናል፡፡ ሀገራችን ከገባችበት የፖለቲካ ችግር እንድትወጣ የተቃዋሚ ሀይሎች ያቀረቡትን የመፍትሄ ሀሳብና ለህዝብ ደምፅ መከበር ስለሚያደርጉት ጥረት አጢነናል፡፡ በሰላማዊና በህጋዊ ትግሉ ወደ ፊት ለመቀጠል ኅብረቱ ስለ አቀረበው ሀሳብ የጋራ ውይይት አካሂደናል፡፡

በእነዚህና በሌሎችም ተዛማጅነት ባላቸው የሀገራችን ጉዳዮች ላይ በሰፊው ከተወያየን በህዋላ የሚከተለውን የአቋአም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. **ስለግንቦቱ ምርጫ**

   የመለስ መስተዳደር በመሰረቱ የግንቦት 7ቱን፣ 1997 ዓ.ም ምርጫ የፈቀደው ለአምባ ገነናዊ አገዛዙ የዴሞክራሲ ሽፋን ለመስጠት እንጂ በእርግጥ የህዝቡን ሉአላዊነት ለመቀበል ሰለአልነበረ የምርጫውን ውጤት ሀይል በመጠቀም በማን አለብኝነት አፍኖታል፤ ድርጊቱ በህዝብ ላይ የተፈፀመ የአፈና ወንጀል ሰለሆነ በጥብቅ እናወግዘዋለን፡፡

2. **የመለስ አስተዳደር ስለሚያካሂደው ግድያ፣ እስራትና ሌላም የመብት ረገጣ**

   2.1. የህዘባችን ድምፅ አይሰረቅ በማለት በሰኔ ወር 1997 ድምፃቸውን ያሰሙ ዜጎችን የመለስ መስተዳደር ለሀገር ጠላት መከላከያ በተዘጋጀ ጦር በመጠቀም ጭንቅላት ጭንቅላታቸውን እየመታ ገድሎአል፡፡ ይህንን ኢሰበአዊ ድርጊት አጥብቀን እናወግዛለን፡፡

   2.2. የመለስ ቡድን በሀገራችን ለዲሞክራሲና ለሰላማዊ ለውጥ የሚታገሉ የህብረተስብ ክፍሎችን ሰበብ እየፈጠረ ያስራል፣ ያዋክባል፣ ከየቀያቸውም እንዲሰደዱ ያሰገድዳቸዋል፣ ከላይ እንደተጠቀሰው ይባስ ብሎም ይገድላቸዋል፡፡ ቡድኑ ይህንን የመብት ረገጣና አፈና ባስቸኳይ እንዲያቆም እንጠይቃለን፣ በእየእስር ቤቱ ያጎራቸውን ዜጎች ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታቸው፣ ንብረታቸው ለወደመም መንግስት ካሳ እንዲከፍላቸው እና ከየቀያቸው ተፈናቅለው የተሰደዱትም አንዲመለሱ እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

   2.3. ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደጠየቅነው ሁሉ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ አሁንም በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

   2.4. በምርጫው ሂደትና በድምፅ ቆጠራው ገዜ የመለስ ቡድን የፈፀመውን የህዝብ ድምፅ ስርቆትና መጭበርበርን ሲቃወሙ በግፍ ለተገደሉ ወገኖቻችን ቤተሰቦች መንግስት የደም ካሳ እንዲከፍል፣ ግድያውም በነፃ አካል ተጣርቶ ገዳዮቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ በጥብቅ እንጠይቃለን፡፡ የተቃዋሚዎችና የኢትዮጵያ የሲቪክ ድርጅቶች ለዚሁ ጥያቄ ተግባራዊነት ግፊት እንዲያደርጉ አናሳስባለን.

3. **ስለተቃዋሚዎች ህብረትና ትግል**

   3.1. ኅብረትና ቅንጅት በጋራ በመስራት ህዝባችን ለመብቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲታገልና ደምፁን እንዲሰጥ ያደረጉት የማደራጀት እና የቅስቀሳ ተግባር የሚያሰመሰግናቸውና እኛንም የሚያኮራን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3.2. ወደፊትም አንድነታቸውን የበለጠ አጠናክረው ተቻችለውና ተጋግዘው የህዝባችንን መብት ለማስከበር የእናት አገራችንን ጥቅም በማሰቀደም አንዲታገሉ አደራ እንላለን፡፡

4. የብሔራዊ አንድነት መንግሰትን ምስረታን በተመለከተ

4.1. በቅንጅቱና በኅብረቱ የብሄራዊ አንድነት መንግሰት ምስረታ ጉዳይ በመሰረቱ ሁሉንም ኃይላት የሚያጠቃልልና የሚያሳትፍ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማስፈን የቀረበ ሀሳብ በመሆኑ በሙሉ ድምፅ ደግፈነዋል፡፡

4.2. የመቻቻል ፖሊሲ ስለሌለ ኢትዮጵያ ወደ ባሰ ቸግርና ቀውስ ልትገባ ስለምትችል ከዚህ ቀውስ ሊያድን የሚችል መፍትሄ ፈልጉ በማለት አያሌ የዓለም ህብረተሰብ አባላት ይሰነዝሩት ለነበረውም ጥያቄ መልስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4.3. ይህንን የሽግግር ዘመን መንግሰት ምስረታ የመለስ ቡድን ባሰቸኳይ እንዲቀበለው እንጠይቃልን፡፡

5. ስለ ወደ ፊቱ ትግል

5.1. በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ሁለት ኃይላት መፋጠጣቸውን ተገንዝበናል፣ ማለትም ባንድ በኩል የመለስ ቡድን በምርጫ የህዝቡን ድምፅ አጭበርብሮ አሸነፍኩ በማለት ስልጣን እንደያዘ ለመቆየት ሕዝባዊ ደሞክራሲያዊ ትግሉን ለማፈን ተዘጋጅቷዋል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ መጭበርበሩን አንቀበለውም በማለት ህጋዊ መብቱን ለማስከበር በቆራጥነት ለመታገል ዝግጁ በመሆን ይንቀሳቀሳል፡፡ አያሌ የአለም አቀፍ ኃይላትም ምርጫው በእርግጥ ሰለመጭበርበሩ መመስከራቸውንም ተረድተናል፡፡

5.2. በዚህ የፖለቲካ ሁኔታ የተቀዋሚ ሀይሎች ሁሉ አንድነታቸውን አጠናከረው የህዘቡ ደምፅ ይከበር በማለት መታገል፣ ማታገልና አመራር መስጠት ያለባቸው መሆኑን በጥብቅ እናምናለን፡፡

5.3. ወደ ፓርላማ መግባትም በዚህ ትግል ውሰጥ ከህዝብ ጎን አለመቆም፣ የህዝብ መብት ሲሰረቅና መበቱ ሲታፈን በዝምታ የማየት አቋም መያዝ መሆኑን አጢነናል፡፡ ስለሆነም "በፓርላማው ገብታችሁ ታገሉ፤ በፓርላማ በመግባት እንታገላለን" የሚል አስተሳሰብን የሚያራምዱ ሁሉ አቋማቸውን እንዲመረምሩ እንጠይቃለን፡፡

5.4. ከመለስ ቡድን ጋር የሚካሄደው የትግል ሒደት ፍሬያማ እንዲሆን ትግሉ የመላው ህዘባችን ሰፊና ሀገር አቀፍ ዲሞክራሲያዊ አንቅስቃሴ መሆን ይኖርበታል በማለት ኀብረቱ በሁለተኛው ጉበኤ ያሳለፈውን ወሳኔ ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን፡፡

5.5. የመለስ ቡድን የሰረቀውን የህዝብ ድምፅ ለመመለስ አሻፈረኝ ካለ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለለወጥ የቆሙ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች፣ የሲቪክ ድርጅቶች፣ የሰራተኞች፣ የገበሬዎች፣ የወጣቶች፣ የተማሪዎች፣ የሴቶችና፣ የሌሎችም ህዝባዊና የሙያ ድርጅቶች ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልቶችን በመጠቀም በአንድነት እንዲሰለፉና መብታቸውን ለማስከበር እንዲንቀሳቀሱ በማለት የኅበረቱ ጉባኤ ያቀረበውን ጥሪ እንደግፋለን፡፡

5.6. በዚህ የትግል ሂደት ቅንጅቱ ተባባሪ መሆኑም በጣም አስደስቶናል፡፡

5.7. ኅብረቱና ቅንጅቱ በሃገራችን የህዝብ ድምፅ እንዲከበር፣ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ለሚያከሂዱት ትግል ህዝቡ ያለውን ድጋፍ እንዲገልፅ መስከረም 22፣ 1998 ብሄራዊና አለም አቀፋዊ ሰልፍ እንዲያደርግ በጋራ ያደረጉትን ጥሪ በደስታ እንቀበላለን፡፡

5.8. የኢትዮጵያ ሠራዊት በሀገር ጥበቃ ላይ ብቻ እንዲያተኩርና የመለስ ቡድን በሚያካሂደው የህዝብ መብት አፈና ላይ ተባባሪ እንዳይሆን እንጠይቃለን፡፡

5.9. የአለም አቀፍ ህብረተሰብም በመለስ አገዛዝ የተሰረቀውን የህዝብ ድምፅ ለማስመለስ በሚደረገው ትግል ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንዲቆም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

በቶሮንቶ ከተማ የኢዴፓን ድጋፍ ኮሚቴ